የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አሥራሦስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

13[th] Year No 26.
ADDIS ABABA 15[th] May, 2007

ማውጫ

CONTENTS

አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፫/፲፱፻፺፱ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በጉምሩክ ሕጎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል፣ ለመመርመርና ለመግታት የሚያስችል ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ... ገጽ ፫ሺ፮፻፫

Proclamation No. 523/2007

Agreement between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Italia on Mutual Administrative Assistance for the prevention, investigation and repression of customs offences Ratification Proclamation Page 3603

## አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፫/፲፱፻፺፱

## በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በጉምሩክ ሕጎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል፣ ለመመርመርና ለመግታት የተደረገ ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ ረቂቅ አዋጅ

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መን ግሥትና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በጉምሩክ ሕጎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል፣ ለመመርመርና ለመግታት የሚያስችል የትብብር ስምምነት መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም በሮም ጣሊያን ላይ የተፈረመ ስለሆነ፤

ስምምነቱ መረጃዎችን ለመለዋወጥ የቴክኒክ ሥልጠናዎችን ለማስገኘት እና የኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣንን አቅም ለመገንባት እና ችግሩን ለመቅረፍ የሚያግዝ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲ ያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው ስለሆነ፤

በሕገ መንግሥቱ አንቀጽ ፶፭ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እና /፲፪/ መሠረት ከዚህ የሚከተለው ታውጇል።

## PROCLAMATION NO. 523/2007.

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF ITALIAN ON MUTUALADMINISTRATIVE ASSISTANCE FOR THE PREVENTION, INVESTIGATION AND REPRESSION OF CUSTOMS OFFENCES.

**WHEREAS,** the Agreement, on Mutual Administrative Assistance for the prevention, investigation and repression of customs offences between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Italy was signed in Rome on the 26[th] day of September 2006;

**WHEREAS,** the agreement enables both parties to share relevant Customs information, technical assistance and this in effect helps the Ethiopian Customs Authority to build its Capacity and thereby tackle its problem ;

**WHEREAS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 24[th] day of April, 2007.

**NOW, THEREFORE,** in accordance with Article 55 Sub-Articles (1) and (12) of the Constitution, it is hereby proclaimed as follows:

ያንዱ ዋጋ Unit Price 2.30

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ.ሣ.ቁ. ፹ሺ፩
Negarit G. P.O.Box 80001

## ፩. <u>አጭር ርዕስ</u>

ይህ አዋጅ "የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራ ሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥትና በጣሊያን ሪፐብ ሊክ መንግሥት መካከል በጉምሩክ ሕጎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል፣ ለመ መርመርና ለመግታት የሚያስችል ስምምነት ማፅደቂያ አዋጅ ቁጥር ፭፻፳፫/፲፱፻፺፱" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

## ፪. <u>ስምምነቱ ስለመጽደቁ</u>

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት እና በጣሊያን ሪፐብሊክ መንግሥት መካከል በጉምሩክ ሕጎች ላይ የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በጋራ ለመከላከል፣ ለመመርመር እና ለመግታት እንዲያስችል መስከረም ፲፮ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም ሮም ጣሊያን የተፈረመው ስምምነት ፀድቋል።

## ፫. <u>ስለአስፈፃሚ አካል ሥልጣን</u>

ይህ ስምምነት በሥራ ላይ እንዲውል የማድረግ ሥልጣን ለኢትዮጵያ ጉምሩክ ባለሥልጣን በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

## ፬. <u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>

ይህ አዋጅ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ግንቦት ፯ ቀን ፲፱፻፺፱ ዓ.ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ፕሬዚዳንት

## 1. Short Title

This Proclamation may be cited as the "Agreement between the government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Italia on Mutual Administrative Assistance for the prevention, investigation and repression of customs offences Ratification Proclamation No.523/2007."

## 2. Ratification of the Agreement

The Agreement on Mutual Administrative Assistance for the prevention, investigation and repression of customs offences signed in Rome on the 26th day of September 2006 is here by ratified.

## 3. Power of the Executive organ

The Ethiopian Customs Authority is here by empowered to implement this Agreement.

## 4. Effective Date

This Proclamation shall come in to force up on Publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 15th day of May, 2007**

**GIRMA WOLDEGIORGIS**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት